# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ልዩ ዕትም ቁጥር 2 የካቲት ፳፫ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## <u>ዐድዋ ኢትዮጵያዊነት ናት!</u>

**(የካቲት 23 የዐድዋ 122ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ)**

አዎ! ጥቁር ነን ግና ሰዎች ነን። የዛሬን አያድርገውና "ነጫጭባ" እያልን ነበር ነጭን የምንንቀው። ንቀታችንም ምክንያት አልባ አልነበረም። በስልጣኔ በመራመዳቸው ቅናት ይዞን አልነበረም። የእኛ ድህነት ስድብ አውርሶን አይደለም። አዎ! አድራጎታቸው፣ ተግባራቸው፣ ምግባራቸው እንዲናቁ አድርጓቸው ነበር። ድህነታችንን ይዘን፣ ድንቁርናችንን ያልፋል ብለን፣ ሕመማችንን ዋጥ አድርገን "አትንኩን!" ብለን ኖርን እንጂ፤ የሰው ቤት አልቀላወጥን፣ ልንሰርቃቸው አልሄድን። የተገላቢጦሽ "ተናጋሪ እንሰሳ"፣ "ቆሞ ሚሄድ አውሬ"፣ "የሰው ከብት" አድርገው ስለውን ሊቦጠቡጡን፣ ሊዘርፉን፣ አህጉር አቋርጠው፣ ውቅያኖስ ተሻግረው መጡብን። እንደ መጽሐፉ "ጥረው ግረው በላባቸው" ሳይሆን ወረው፣ ዘርፈውና ቀምተው ሊበሉ፣ ሊበለጽጉ የሰው ቤት ሲያንኳኩ፣ እንደ ምስጥ አፈር ሲሸረሽሩ "ነጫጭባ" ቢባሉ ምን ያስደንቃል?

የዛሬ 122 ዓመት ገደማ በዓለማችን አደግን፣ በለጸግን ያሉ ሃያላን መንግስታት የየሀገራቸውን ውስጥ ችግር ለመፍቻና እነሱ ደልበው ሌላ ይራቆት ዘንድ አፍሪካን አነጣጥረው ወረሯት። የዓለም ታሪክ የወራሪና ተወራሪ ነበር። የዓለም ታሪክ የቅኝ ገዥና ተገዥ ታሪክ ነበር። የራሱን የተፈጥሮ ሀብት ለክፉ ቀን አስቀምጦ የሌሎችን መመኘት፣ መጎምዠት። ሀገራቸውን ለማልማት በባርነት ስም የሰው ልጅን ወደ ሀገራቸው ማጋዝ፣ አፍሪካ ለእነሱ የተቀመጠች አንጡራ ሀብት፣ የበለጸጉቱ ተመራርጠው የሚከፋፈሏት የቅርጫ ሀገር፣ በሰው ሀገር ባንዲራቸውን ሰቅለው የራሳቸውን ባህል፣ ቋንቋ፣ አስተዳደር፣ . . . ፖለቲካ በምስኪኑ የአፍሪካ ሕዝብ ላይ በመጫን እስከዛሬ ጠባሳው ያለቀቀ መርዝ የበተኑበት ዘመን። በሀገሮች ህብረት (League of Nations) ዘንድ ወረራ ሕጋዊነት ያስመዘገበበት ዘመን። አፍሪካ፣ ጥቁር ሕዝብ አሜን ጸጥ ለጥ ብሎ የ40 ቀን ዕድሉን መቀበል ብቸኛው አማራጭ ተደርጎ የተሰበከበት አስከፊ ዘመን። ይህ ነበር የዓለማችን ውብት 100 ዓመት መለስ ብለን ስንጓዝ።

የኢትዮጵያ ሀገራችን የሦስት ሺህ በላይ ዘመን ታሪክ ከዘመነ አክሱም ወደ ዛጉዬ፤ እንደገና በይኩኖ አምላክ አማካይነት ወደ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ሲሸጋገር ኑሮና በ1700 ዎቹ ዘመነ መሳፍንትን በትንሹ ለ200 ዓመት አስተናግዳለች። ይህችን በተለያዩ መሳፍንት የተበታተነች ኢትዮጵያን ወደ አንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ለማምጣት መሠረት በመጣል ሁሌም ስማቸው የሚጠቀሰው ዓፄ ቴዎድሮስ ድርሻ ቀላል አልነበረም። አፄ ቴዎድሮስ የውጭ ባዕዳንና ወራሪዎችን እንደተከላከሉና በመጨረሻም በውስጥም በነበረባቸው ችግር ሀገር ምን ማለት እንደሆነች በደማቸው መቅደላን አደመቁ። የእንግሊዝ ወራሪን አሳፈሩ።

*"ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው፤*

*ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው፤*

*ምናሉ እንግሊዞች ሲገቡ ሀገራቸው፤*

*ለወሬ አይመቹ ተንከለኞች ናቸው።"*

ያሰኙት የቋራው ጀግና የኢትዮጵያን አንድነት መሠረት ጥለውና ታሪክ ሰርተው እስከዛሬም ወደፊትም ይዘመርላቸዋል።

አፄ ዮሐንስ በቀጣይነት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ዳር ድንበር ከወራሪ በመከላከልና እንደ አሉላ አባ ነጋ ጠላት ላይ ሠፋሪ፤ ዶጋሌ መስክራ ኢትዮጵያችን ታፍራና ተከብራ ስትኖር መተማ ላይ ለአንድነቷና ለሉዓላዊነቷ ያጣችውን አፄዋን ዮሐንስን ምንጊዜም አትረሳም።

ኢትዮጵያ ከጥንት በግዕዝ መሠረቱን ያደረገው ቋንቋዋ ሳይበረዝ፣ የተለያዩ አኩሪ ባህሎቿ እንደተጠበቁ፣ ሃይማኖቷ ሳይበረዝ፣ ትጓዝ ዘንድ የጥቁር ሕዝብ ጀግና ምኒልክን ወለደች።

በ1836 ዓ.ም. በአንኮበርና ደብረብርሃን መካከል አንጎለላ ከሚባል የገጠር መንደር የተወለዱት አፄ ምኒልክ አባታቸው ከሰሎሞን ሥርወ መንግስት የመጡ ንጉሥ ሃይለመለኮት እናታቸው ወ/ሮ እጅጋየሁ ናቸው።

ከአፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ኅልፈት በኋላ ምኒልክ በጥቅምት 1882 በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው "*ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*" ተብለው ነገሡ።

አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አስከብረው፤ ኢትዮጵያ ወደ ዕድገትና ስልጣኔ ጎዳና ታመራ ዘንድ ዕቅዳቸውን ነደፉ። በውጭ ዲፕሎማሲው በኩልም በገለልተኝነትና በሰላም የከበቧቸውን ባዕዳን ወራሪዎች ትኩረት በመስጠት ተጓዙ። ለዐድዋ ጦርነት መነሻ የሆነውን በሀገራት መካከል የተደረገ ስምምነት ከኢጣልያን ጋር ተዋዋሉ። ውሉም የውጫሌው ውል በመባል ይታወቃል። በዚህ 24 አንቀጽ በያዘው ውል አንቀጽ 17 "*ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥገኝነት ሥር እንዳለች*" ሆን ተብሎ ተዛብቶ የተቀመጠው የኢጣልያንኛ ትርጉም ለውሉ መፍረስ ምክንያት ሲሆን ጣሊያንም ኢትዮጵያን ለመውረርና ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ ካላት ትልም አንፃር የኢትዮጵያን ግዛት እየሰረሰረች ሠራዊቷን ዐድዋ ላይ አከማቸች።

የሀገሬን ዕልውና ለባዕድ ወራሪ አሳልፌ አልሰጥም ብለው የውጫሌን ውል መሠረዙን ያሳወቁት ምኒልክ ለቀጣይ ኢትዮጵያ "ያገሬ ሰው!" ብለው ድምጻቸውን አሰሙ። ከአራቱም የሀገሪቷ ማዕዘን ጥሪያቸውን የተቀበለው ሕዝብ ምኒልክ ከተሀ ላግኝህ ባሉት ወረይሉ እየፎከረና እያቅራራ ትዕዛዛቸውን ይጠባበቅ ጀመር። የቤት እመቤቶች በስንቅና ትጥቅ ሠራዊቱን ተከትለው ነጎዱ።

እነሆ ልክ የዛሬ 122 ዓመት የኢትዮጵያ ሠራዊት ወራሪው የጣልያን ሠራዊት ላይ ዘነበበት። ቀፎው የተነካ ንብ ማር ቆራጩን ወራሪ ጠላት "ሲያምርህ ይቅር" በሚል ጀግንነት ደመሰሰው። በዕለተ ጊዮርጊስ እንደእምነታቸው ታቦቱን ይዘው የተጓዙት ምኒልክ ጠዋት የተጀመረው ጦርነት ረፋዱ ላይ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቋል። የሰው ቤት ሊያንድ የመጣው ወራሪ ነዶና ዓመድ ሁኖ ተበተነ። ደረቱን አሳብጦ የገባው ሠራዊት አንገቱን አቀርቅሮ ተባረረ። ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ለሀገሩ ክብር፣ ለነፃነቱ ጥቁረቱ ምልክት እንዳልሆነ አሳየች። የዐድዋን ድል የዐለም ጥቁር ሕዝቦች ድል

እንደሆነ አስመሰከረች። በእናትና አባቶቻችን ክቡር መስዋዕትነትና ተጋድሎ የተገኘው የዐድዋ ድል በቅኝ ገዥዎች ላይ የነበራቸውን ግፍና ህልም በአጭር ያስቀረ አንጸባራቂ ድል ሆነ።

ኢትዮጵያ-አድዋ-ምኒልክ አንድም ሦስትም ሆኑ። "ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!" ሲባል ዐድዋ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ዐድዋ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። በዐድዋ ምድር የደቡብ፣ የምዕራብ፣ የምሥራቅ፣ የሰሜን ወገኖቻችን ደም አለ። ዐድዋ ኢትዮጵያን የማዳን ዕምብርት ናት፣ ዐድዋ የጀግኖች መቃብር ናት፣ ዐድዋ የሰማዕታት ሐውልት ናት፣ ዐድዋ እምነት ናት፣ ዐድዋ ጽናት ናት፣ ዐድዋ ኢትዮጵያዊነት ናት፣ ዐድዋ ምኒልክ ናት።

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ለ122ኛው የዐድዋ ክብረ በዓል እንኳን አደረሳችሁ እንላለን። ዐድዋን ስናከብር ኢትዮጵያን እናስባለን፣ ጀግኖቻችንን እንዘክራለን፣ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ እናደርጋለን፣ ሰንደቅ ዓላማችንን እናውለበልባለን። ወረራና ዝርፊያ አስከፊነቱን ትውልድ ይማርበት ዘንድ ዐድዋ ትምህርት ቤት ናት፣ ዐድዋ ቤተ መዘክር፣ ዐድዋ ልቅሶ ናት፣ ዐድዋ ዕልልታ ናት፣ ዐድዋ ፉከራ ናት፣ ዐድዋ ክብር ናት፣ ዐድዋ ማንነታችን ናት።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በተለይ ለአለፉት 27 ዓመታት እየገዛት ያለው ህወሓት/ኢሕአዴግ ዓይነት በሀገርና በሕዝብ ህልውና ላይ የመጣ አገዛዝ አጋጥሟት አያውቅም ቢባል ማጋነን አይደለም። ዛሬ ስለ መበዝበዝ ብቻ ሳይሆን ስለ መፈረካከስ እያወራን ነው። የዛሬ 122 ዓመት በጦርና በጎራዴ እስካፍንጫው የታጠቀን ወራሪ ጠላት ድባቅ የከተቱ ጀግኖቻችን ክብራቸው በከሀዲ የሀገር ባንዳዎች እየተረገጠ ነው። ወያኔ ዐድዋን ሊያቃጥላት ነው፣ ወያኔ ዐድዋ ላይ ዘምቷል። ኢትዮጵያውያን ዘር፣ ቋንቋና ሃይማኖት ሳይለያቸው ተቃቅፈው ተዋግተው፣ ተቃቅፈው ያሸለቡባትን ዐድዋ ከታሪክ ማህደር ሊያጠፉት መጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል።

***"ያገሬ ሰው!"*** እንዳሉት ምኒልክ ***የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!*** እንላለን ዛሬ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ሊበታትን፣ የሃይማኖትና የዘር ጦርነት እርስ በርሳችን እንዲነሳ ተልዕኮው የሆነው ወያኔ እስከዛሬ በመንግስትነት እያወናበደ ሲገዛህ፣ ሲያተረማምስህ፣ ሲገርፍህ፣ ሲያሰድድህ፣ ሲገድልህ ኖሯል። አሁን ግን ሊበቃ ይገባል። በአንድ ቀን ተጀምሮ በአንድ ቀን የተጠናቀቀውን የዐድዋ ድል በመድገም ዳግም ዐድዋን ልናድሳት ይገባል። ለሀገርህና ለራስህ ህልውና ያለምንም ጥያቄ ወያኔ/ህወሓት ላይ አቅም ያለህ በጉልበትህ አቅም የሌለህ በፀሎትህና በሀሳብህ ዘር፣ ቋንቋ፣ ክልል፣ ዕድሜ፣ ፆታና ሃይማኖት ሳይለይህ ተነስ! ዐድዋን በየዓመቱ መዘከር ብቻ ሳይሆን ታሪክ መሥርያ እናድርጋት። ከእናት አባቶቻችን የወረስነውን ጀግንነት ሀገር አጥፊው ወያኔ ላይ እናሳርፈው። ድሉ የኛው ነውና!

***ለኢሕአዴግ አጋር ድርጅቶች !*** አብዛኛው ሕዝብ ከወያኔ/ህወሓት ነጠል በማድረግ ሁኔታዎችን ታስተካክላላችሁ፣ ወያኔ/ህወሓትን አስወግዶ ለመሠረታዊ ለውጥም በር ትከፍታላችሁ በሚል የነበረው የተስፋ ጭላንጭል እንዳይሟጠጥ ያሰጋል። ህውን ለዚች ሀገር አንድነትና ለሕዝባችን አብሮ መኖር ቁርጠኝነትን ምታሳዩበት ወቅቱ ዛሬ ነው። በዛሬው የዐድዋ 122ኛ ክብረ በዓል የኢሕአዴግ ምክር ቤት ስብሰባውን እንደሚያካሂድ ይታወቃል። የዚህም ስብሰባ ዋና ጉዳይ በቅርቡ ለሦስተኛ ጊዜ የወጣውን የወያኔ/ህወሓት ገዳይ አዋጅ *"አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ"* የኢሕአዴግ ምክር ቤት እንዲያጸድቅ ይጠበቃል። ይህን አዋጅ ከህወሐት/ወያኔ አባላት በቀር ሁላችሁም አጋር ድርጅቶች ውድቅ በማድረግ ታሪክ ሰርታችሁ ከኢትዮጵያ ሀገራችሁና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም ማንነታችሁን የምታሳዩበት ወሳኝ ቀን ነው።

ይህንን ተራና አፋኝ አዋጅ ለወያኔ/ህወሓት ተባብሮ ማጽደቅ ማለት በኢትዮጵያ ሕዝብና ልጆቹ ላይ በሚካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋና ዕልቂት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነታችሁን ነጋሪ አያስፈልጋችሁም። ይህንን አዋጅ በግልም ሆነ በተሰለፋችሁበት ድርጅት ድጋፍ በመስጠት አጸደቃችሁ ማለት በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጥፋት ሙሉ ሃላፊነት ወስዳችኋል ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁሉም አቅጣጫ ወያኔን ወጥሮ ወደ መቃብሩ ሊወረውረው በተዘጋጀበት ወቅት እናንተም የምታጡት ቢኖር ዘረኛውንና ሀገር አጥፊውን ወያኔ/ህወሓትን ነውና ሳታቅማሙ ድጋፋችሁን በመንሳት ሕዝባዊነታችሁን ይፋ አውጥታችሁ ከሕዝባችሁና ሀገራችሁ ጎን ትቆሙ ዘንድ የመጨረሻው ዕድላችሁን ተጠቀሙበት ስንል *“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”* አበክረን እንገልፃለን።

***የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ ተማሪዎችና፣ ሴቶች !*** የወደፊቷ ኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ያለው በቀጣዩ በእናንተ ወጣቶቹ ላይ ነው።፡ ሀገርን የማዳን ብቻ ሳይሆን የመረከብ ኃላፊነት አለባችሁ። የዛሬ 122 ዓመት በዐድዋ ታሪክ ሰርተው ያሸለቡ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በአፈሰሱት ደም፣ በከሰከሱት አጥንት ኢትዮጵያን ለትውልድ አስተላልፈዋል። አደራ አለባችሁ። ተተኪ ትውልድ አጠፋም አለማ ሀገሩን ተረክቦ ለሀገሩ ያለውን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ ይጥራል። በሌላም በኩል ይዞ የተነሳው ዓላማ ግብ ያልመታለትም ትውልድ አለ። ይህን ሁላ ሀገር ይዛ ተጉዛለች። ትውልድ ይመጣል፣ ትውልድ ይሄዳል ሀገር ግን ዘላለማዊ ነች። አሁኑ ትውልድ ላይ የደረሰች ሀገር በርካታ ችግሮችንም ተሸክማ ነውና ኃላፊነታችሁ ቀላል አይደለም። ቀዳሚው ግና ይህች ሀገራችን ሊያጠፉት የቋመጠው ወያኔ/ህወሓት እና የውጭ ባዕዳን ኃይሎች እጅ ሳትወድቅ ከአለው አገዛዝ ለማላቀቅ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። በሀገሪቷና በየአካባቢው የምታደርጉት እንቅስቃሴ ተጠናክሮና ተቀናጅቶ ለድል ይበቃ ዘንድ “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!” ብላችሁ በሞታችሁ ሀገራችሁን አድኑ።

የዐድዋ ሰማዕታት ለኢትዮጵያ አንድነት!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”

የካቲት 23 ቀን 2010 ዓ.ም. (March 02, 2018)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen